መልእክት አሥር

# ክርስቶስ—የመንግሥቱ መሥራች
# እና
# የእግዚአብሔር ቃል—የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 20፥1-6፤ 19፥11-16፣ 19-21

## I. ክርስቶስ የመንግሥቱ መሥራች ነው—ራእ. 20፥1-6፦

ሀ. ጠላቶቹን ከተዋጋ በኋላ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት፣ የሺህ ዓመቱን መንግሥት በምድር ላይ ይመሠርታል፣ ድል ከሚነሡ አማኞቹም ጋር ለሺህ ዓመት ይነግሣል—ቁ. 2።

ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት ለመምጣቱ እንደ ዝግጅት መላው ምድር መጽዳት አለበት።

ሐ. አንድ ነገር ብቻ ይቀራል፣ እርሱም የችግሮች ሁሉ ምንጭ የሆነው ሰይጣን ነው።

መ. የሺውን ዓመት የሚመለከት ምዕራፍ በሆነው በራእይ 20 የተጠቀሰው የመጀመሪያው ነገር የሰይጣን መታሰር ነው፦

1. ምንም እንኳን ጌታ በመስቀል በሰይጣን ላይ ቢፈርድበትም፣ ያ ፍርድ እስካሁን ድረስ ሙሉ በሙሉ አልተፈጸመም።
2. ጌታ ሲመለስ፣ በመስቀል ላይ በሰይጣን ላይ የፈጸመውን ፍርድ ሙሉ በሙሉ ይፈጽማል።
3. ሰይጣን ምንም ለማድረግ ወይም ማንንም ለመጉዳት ኃይል የሌለው ሆኖ ታስሮ ወደ ጥልቁ ይጣላል፤ ያኔ ምድር የክርስቶስ መንግሥት ትሆናለች።

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች መሠረት፣ ሺው ዓመት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፦ የላይኛው፣ ሰማያዊው ክፍል እና የታችኛው፣ ምድራዊው ክፍል፦

1. የሺህ ዓመቱ የላይኛው ክፍል የአብ መንግሥት ይባላል (ማቴ. 13፥43)፣ የታችኛው ክፍል ደግሞ የሰው ልጅ መንግሥት ይባላል (ቁ. 41)።
2. የመሲሑ መንግሥት፣ ወይም መሲሐዊው መንግሥት፣ ለሺህ ዓመቱ የታችኛው ክፍል ሌላ ስም ነው።

ረ. ራእይ 20፡4-6 ክርስቶስ እንደ የመንግሥቱ መሥራች ድል ከሚነሡት ቅዱሳን ጋር እንደሚነግሥ ይገልጣል፦

1. ድል ነሺዎቹ የኢየሱስ ክርስቶስን መንግሥት ስለሚያመጡ፣ ጌታ ለሺህ ዓመት ይነግሣል፣ ድል ነሺዎቹም ደግሞ ከክርስቶስ ጋር ለሺህ ዓመት ይነግሣሉ።
2. ራእይ 20፥4 "ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው" ይላል፦
   - ሀ. *ለተቀመጡት* በሚለው ቃል ውስጥ የተመለከተው ተውላጠ ስም ድል ነሺዎቹን ያመለክታል።
   - ለ. አሁን በዙፋኖች ላይ ተቀምጠዋል፣ የመፍረድ ሥልጣንንም ተሰጥቷቸዋል።
     1) የመፍረድ ሥልጣን ማግኘት ማለት መንግሥቱን ማግኘት ማለት ነው—ዳን. 7፥10፣ 18፣ 22።
     2) በራእይ 20 ቁጥር 4 ድል ነሺዎቹ መንግሥቱን እንደተቀበሉ እና እየተደሰቱት እንደሆነ ያመለክታል።

ሰ. ድል ነሺዎቹ የኢየሱስ ስብዕና ወደ እነርሱ ውስጥ በመሠራቱ ከክርስቶስ ጋር ለመንገሥ ብቁ ይሆናሉ—2፥26።

ሸ. በሺህ ዓመቱ ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት ድል ነሺዎች ምርጡን ትንሣኤ ይደሰታሉ፦

1. ራእይ 20፥6 ስለ "ፊተኛው ትንሣኤ" ይናገራል።
2. የፊተኛው ትንሣኤ "የላቀው-ትንሣኤ" ነው፣ ማለትም፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ይፈልገው የነበረው እጅግ የላቀው ትንሣኤ ነው—ፊልጵ. 3፥11።

ቀ. ራእይ 20፥6 "በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው" ይላል፤ ይህ በምድር ላይ የተገለጠውን መንግሥት መውረስ፣ ብሎም በውስጡ ነገሥታት መሆን ከፍተኛው በረከት መሆን አለበት።

በ. "የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺ ዓመት ይነግሣሉ" (ቁ. 6)፤ ድል ነሺዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ካህናት፣ በሺው ዓመት በሕዝብ ላይ ይነግሡ ዘንድ ከክርስቶስ ጋር አብረው የሚነግሡ ይሆናሉ (2፥26-27፤ 12፥5)።

## II. በራእይ 19፥11-16 እና 19-21 ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል—የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ—ተገልጧል፦

ሀ. ከሰርጉ ድግስ በኋላ (ቁ. 7) ክርስቶስ እንደ ተዋጊ ጄኔራል ከሙሽራይቱ፣ ሠራዊቱ ከሆኑት ድል የሚነሡ አማኞች ጋር የክርስቶስን ተቃዋሚ ለመዋጋት ይመጣል፤ ሰውም እንኳን ሳይቀር ከጌቶች ጌታና ከነገሥታት ንጉሥ ጋር በቀጥታ ውጊያ ይገጥማል፦

1. የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ሐሰተኛው ነቢይ እና አሥሩ ነገሥታት እና ሠራዊቶቻቸው ከበጉ ጋር ውጊያ ይገጥማሉ።
2. ይህ ጦርነት ምድር ከሰማያት ጋር፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርገው ውጊያ ይሆናል።
3. የክርስቶስ ጠላቶች በእርሱ ላይ ጦርነት በማወጅ ጭምር ይበልጥ ከፉዎች ይሆናሉ።
4. ሰው በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት ማወጁ በእርግጥም እጅግ የሚያስደንቅ ነው።
5. ሙሽራው ክርስቶስ እነርሱን ለመዋጋት ከሙሽራይቱ ጋር ይመጣል።

ለ. "እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም"—ቁ. 11፡-

1. *የታመነ* እና *እውነተኛ* የክርስቶስ መጠሪያ ይሆናል።
2. ክርስቶስ ለእግዚአብሔር እና በእርሱ ለሚያምኑት የታመነ ነው።
3. በታማኝነቱ እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን እና አማኞችን የሚያሳድዱትን ያሸንፋቸዋል፣ ያጠፋቸውማል።
4. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በማከናወን እና በእርሱ የሚያምኑትን በመንከባከብም እውነተኛ ነው።

ሐ. ክርስቶስ በነጭ ፈረስ ላይ የሚቀመጠው፣ በጽድቅ የሚፈርደው እና የሚዋጋው የእግዚአብሔር የታመነ እና እውነተኛ ምስክር ነው፡-

1. ክርስቶስ ዛሬ በዓለም ውስጥ እንደ የዓመፅ ምሥጢር የሚሠራውን እና የዓመፅ ሰው የሆነውን የክርስቶስን ተቃዋሚ የሚያመጣውን የሰይጣንን የዓመፅ ኃይል ለመዋጋት ተመልሶ ይመጣል—2 ተሰ. 2፥3፣ 7-8።
2. መላው ዓለም በሰይጣናዊው የዓመፅ ኃይል ሥር ነው።
3. ክርስቶስ በክርስቶስ ተቃዋሚ እና በአጋሮቹ ሁሉ የሚደረግውን ዓመፅ በጽድቅ ለመዋጋት ተመልሶ ይመጣል።
4. ክርስቶስ በጽድቅ መፍረድ ብቻ ሳይሆን በጽድቅም ይዋጋል፤ በመዋጋት ይፈርዳል።

መ. "ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል"—ራእ. 19፥13፡-

1. ይህ የሚያመለክተው ጌታ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ነው።
2. የጌታ ስም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ መጠራቱ እርሱ የእግዚአብሔር መገለጥ፣ ምስክር እና ንግግር ነው ማለት ነው።
3. የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ፍቺ፣ መብራራት እና መገለጥ ነው።
4. እግዚአብሔርን ለማወቅ፣ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ፣ ማጥናት፣ ማስተዋል፣ በጥልቀት ማሰላሰል እና አተኩሮ መመልከት ያስፈልገናል።

ሠ. በራእይ 19 እንደ የእግዚአብሔር ቃል፣ ክርስቶስ በዓመፀኞቹ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ በመፈጸም ለእግዚአብሔር ይናገራል፡-

1. ጌታ ሲዋጋ እንኳን ሳለ፣ ለእግዚአብሔር ይናገራል፣ እግዚአብሔርንም ይገልጣል።
2. እግዚአብሔር የግራ መጋባት አምላክ አይደለም፤ እርሱ ጻድቅ እና ሉዓላዊ ነው፤ ደግሞም የስርዓት አምላክ ነው፣ ስለሆነም፣ ስርዓት አልበኝነትንና ዓመፅን ሊታገሥ አይችልም።
3. ክርስቶስ ከጠላት ጋር ሲዋጋ ሳለ፣ እግዚአብሔር ሉዓላዊ፣ ጻድቅ እና ስርዓት ያለው እንደሆነ ይናገራል።
4. እግዚአብሔር በሁሉም ላይ አምላክ እንደሆነ እና በሥልጣኑ ላይ ማመፅን እንደማይታገሥ ያውጃል።
5. ተዋጊው ቃሉ ነው፤ ውጊያውም የእግዚአብሔር ቃል መነገር ነው።
6. በአርማጌዶን ጦርነት ላይ የጌታ ውጊያ ኃይለኛ ንግግር ይሆናል፡-
    ሀ. ለሰይጣን፣ ለክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ለሐሰተኛው ነቢይ እና ለመላው አጽናፈ ዓለም እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንደሆነ እና ማንም በእርሱ ላይ ሊያምፅ እንደማይችል ይናገራል።
    ለ. የስርዓት አምላክ ዓመፅን ሁሉ ጠርጎ ያስወግዳል።

**III. ክርስቶስ ምድርን የራሱ ካደረገ በኋላ፣ በመንግሥቱ ውስጥ በምድር ላይ እንደ ንጉሥ ይነግሣል፣ ድል ነሺ ከሆኑት አማኞቹም ጋር አሕዛብን ይገዛል—20፥4፣ 6፤ 2፥26-27፡-**

ሀ. እንደ የሚመጣው ንጉሥ፣ በሺው ዓመት በሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ራስ እና ማዕከል ይሆናል።

ለ. ይህ የኢሳይያስ 32፥1፣ የኤርምያስ 23፥5 እና የዘካርያስ 14፥9፣ 17 ፍጻሜ ይሆናል።

ሐ. ክርስቶስ ምድርንና ሕዝቦቿን በሙሉ የመንግሥቱ ከበብ እና ክፍሎች እንዲሆኑ ዋጅቷል (ቆላ. 1፥20)፣ መንግሥቱን ለመግዛት ሁሉን ሸጧል (ማቴ. 13፥44)፣ ምድርንም ከሕዝቦቿ ሁሉ ጋር ከሰይጣን አለአግባብ መያዝ አድኗል (ራእ. 20፥2-3)።

መ. የታደሰችው ምድር እና የተመለሱት አሕዛብ ንጉሥ የመሆን ሙሉ መብት ይኖረዋል።

ሠ. በሚመጣው ግዛቱ የእግዚአብሔር ሥልጣንና ክብር በሙላት ይገለጣል (ማቴ. 6፥13)፣ ምድርም ሁሉ ከሕዝቦቿ ሁሉ ጋር ወደ ጽድቅ፣ ሰላም፣ ደስታ እና የእግዚአብሔር ፍጥረት ሙሉ በረከት ውስጥ ይገባሉ (ኢሳ. 32፥1፣ 16-18፤ 35፥1-2፣ 5-7)።

*© 2025 Living Stream Ministry*